# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**መስከረም 13 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ወያኔ የጀመረውን የጅምላ አፈሳ በመፍራት ዜጎች እየተሰደዱ መሆኑ ተጋለጠ፤**

**በዜጎች ላይ የሚደርሰውን ግፍ እና ስቃይ ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ ዲፕሎማቶች ማስረጃ እየያዙ መሆኑ ተጠቆመ፤**

**ወያኔ የገዛ ካድሬዎቹን እየመነጠረ ነው ተባለ፤**

**መከላከያም ሊታመስ መሆኑ ተጠቆመ፤**

የወያኔ ቡድን ህዝቡን ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ከትቶ እንዳይናገርና እንዳይተነፍስ ከማድረጉም በተጨማሪ በፍርሀት እየራደ እንዲኖር አዲስ በነደፈው ስልት መሰረት በተለይ ከአዲስ ዓመት መባቻ ጀምሮ ከፍተኛ የጥርጊያ ዘመቻ እያደረገ በመሆኑ እጅግ ቁጥራቸው የበዛ ዜጎች ወደ ጎረቤት ሀገራት እና አውሮፓ እየተሰደዱ መሆኑ ታወቀ::

መላው የሀገሪቱ ዜጎች በወያኔ ድንገተኛ አፈሳ በመደናገጥ ጠዋት ከቤቱ ሲወጣ ማታ መመለሱን እርግጠኛ ባለመሆኑ አምላኩን እየለመነ እንዲያም ሲል የቅርብ ዘመድ እና የሚተዋወቁ እርስ በርስ አንዱ አንዱን እየጠበቀ የእለት ጉርሱን ለመሸፈን ከላይ እስከ እታች ከልተማረው እስከ ምሁሩ...... ከደሀው እስከ ሀብታሙ ድረስ በጭንቀት ተውጦ ያለበት ደረጃ በመድረሱ ዜጋው ሁሉ ስደትን አማራጭ ማድረጉ ታውቆዋል::

በጭንቀት ውስጥ ያለው የሀገሪቱ ዜጋ ሁሉ በድንገት በወያኔ አፋኝ ቡድን ቢታፈስ ለቤተሰብ እንዲነግርለት በማሰብ አንዱ አንደኛውን እየጠበቀ እርስ በርስ ከመተያየት ባሻገር ፍርሀቱ በፈጠረበት ችግር ምክንያት አተኩሮ የሚያየውን ሰው ሁሉ እንደ ሰላይ ኮብራዎች በመፍራት

ወደማይፈልገው አቅጣጫ ለመሄድ እስከሚገደድበት ድረስ መድረሱም የአፈና አገዛዙ የፈጠረው ማነቆ መሆኑን ዜጎች እየተነጋገሩበት ይገኛሉ ።

ከያሉበት እየታፈሱ ወደ እስር ቤት የሚገቡት ዜጎች ቁጥር ከመብዛቱ የተነሳ እስር ቤቶች በመጨናነቃቸው ከህዝቡ ላይ እየዘረፉ እና እየቀሙ ለእስር የተዳረጉትን የዘንቢል ሌቦችና ኪስ አውላቂዎች ብቻ ተመርጠው ከየእስር ቤቱ እየተለቀቁ በምትካቸው ዜጎች በአመለካከታቸው ብቻ እየታደኑ በሽብርተኝነት ስም እየታጎሩ ይገኛል።

በተለይ የወያኔን ቡድን በቀጥታም ሆነ በአደባባይ ሲነቅፉ የነበሩ ዜጎች ሰሞኑን በተጀመረው የጅምላ አፈሳ ዘመቻ በመደናገጥ እና በመፍራት በየጎረቤት ሀገሩ አልፎ ተርፎም ወደ አውሮፓ መሰደድ አማራጭ በማድረግ በስፋት በመጉዋዝ ላይ መሆናቸው እየተሰማ ነው።

በየሳምንቱ ቅዳሜ እየታተመች ለንባብ የምትበቃ የነበረችው የአዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጆችን በሽብርተኝነት ወንጀል ሊከስሱዋቸው ሽመልስ ከማል እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት መምሪያ በጋራ በምስጢር ሰበብ እያዘጋጁ መሆኑን የሰማው ጋዜጠኛ አርጋው አሸኔ ለአዘጋጆቹ በመናገሩና ጋዜጠኞቹም ማምለጣቸውን ተከትሎ ወያኔ አድኖ ዘብጥያ ሊከተኝ ይችላል በሚል ፍርሀት ሀገር ጥሎ ሊሰደድ እንደቻለ ለማወቅ ተችሎዋል።

ጊዜ የሰጠው የከተማው ታጋይ የሆነው ሽመልስ ከማል በአሁኑ ሰዓት እየተያዙ ለእስር የሚዳረጉ ዜጎችን እያንቁዋሸሸ እና ክብራቸውን በሚነካ መልኩ እያዋረደ ፍፁም ኢትዮጵያዊነት በጎደለው ቁዋንቁዋ እየተሳደበ ከመሆኑም በላይ ገና ብዙ የሚታፈሱ ዜጎች እንዳሉ በይፋ እየገለፀ በመገኘቱ ዜጎች በፍርሀት እየተሰደዱ ይገኛሉ።

ለሀገር እና ለወገን የሚጠቅሙና ሊሰሩ የሚገባቸው ዶክተሮች፣መሀንዲሶች በአጠቃላይ ምሁራኖች ወያኔ በሚያደርገው የጅምላ አፈሳ በመፍራት ከወገናቸው እንዲሁም ከሚወዱዋት ሀገር ጥለው ስደት ከመግባታቸውም በተጨማሪ ቤተሰቦቻቸውን ለዘመዶቻቸው አደራ እየሰጡ እንደሆነም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

በዚህም የተነሳ ለብዙ ዓመታት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ሲያስተምሩ የነበሩና የወያኔ ስርዓት በህዝብ እና በሀገር ላይ የሚሰራውን ሸፍጥ ሁል ጊዜ ሲቃወሙ የነበሩ ሶስት ምሁራኖች ሀገር ጥለው መሰደዳቸው ተጋልጦዋል።

ቤተሰቦቻቸው ለግዜው ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉት እነዚሁ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራኖች በስብሰባ ሰበብ ከኢትዮጵያ ወጥተው ወደ ተለያዩ ሀገራት የተጉዋዙ ሲሆን የወያኔ ስርዓት እስካልተወገደ ድረስ ዳግመኛ ወደ ሀገር ቤት እንደማይመለሱ ቤተሰቦቻቸው እና የቅርብ ዘመዶቻቸው ሲገልፁ ተደምጠዋል።

ለሀገር እና ለህዝብ የሚጠቅሙ ዜጎችን የሚያፈራ ተቋዋም የሆነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲና ሌሎቹም አዳዲስ ተቋዋሞች በፖለቲካ ተተብትበው የሚፈለገው ውጤት ያለመምጣቱን ሲቃወሙና ሲተቹ የነበሩት እነዚህ ምሁራን በወያኔ የደህንነት ኃይሎች ጥብቅ ክትትል ሲደረግባቸው

እንደነበሩ የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በተለይ ሰሞኑን በዜጎች ላይ እየተፈፀመ ባለው የሽብርተኛ ዘመቻ ሰበብ ለእስር ሊዳረጉ እንደሚችሉ ስጋት ስለገባቸው በተለያዩ ሀገራት ጥናት እና ስብሰባ በሚል ከሀገር ወጥተው ሊሰደዱ እንደቻሉም ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል።

በጎሳ ላይ የተመሰረተው የወያኔ ፖለቲካ ለሀገርም ሆነ ለህዝብ የማይጠቅም ይልቁንም ትውልዱን የሚከፋፍል እና የሚበታትን መሆኑን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሲገልፁ የነበሩት እነዚሁ መምህራኖቹ ከዚህ ቀደም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቦርድ ሰብሳቢ ከሆነው ጁኔዲ ሳዶ ጋር በተደረገ ውይይት ምሁራኖቹን ፈሪ ......የማስተማር ችሎታ የሌላችሁ......ወረቀታችሁን ለመያዝ ስትሉ ብቻ ሽምድዳችሁ የምታስተምሩ......በማለት ከፍ ዝቅ እያደረገ በተናገረበት ወቅት እነዚህ መምህራኖች በመበሳጨት አንተ የተነገረህን የምታስተላልፍ ቦይ ነህ...... ነጻነት የሌለህ ......በአንድ ግለሰብ ብቻ የምትመሩ.....የመማር ማስተማሩን ትታችሁ ወጣቱን በፖለቲካ ተብትባችሁ እውቀት እንዳያገኝ ያደረጋችሁ የእወቀት ደሀዎች በማለት ምላሽ ከመስጠታቸውም በተጨማሪ የስብሰባ አዳራሹን ጥለው መውጣታቸውን ያስታወሰው የደረሰን ዘገባ እነዚህና ሌሎች ጉዳዮች ተደማምረው ከያሉበት ሊለቀሙ እንደሚችሉ ስጋት ስላደረባቸው ወያኔን ቀድመው ለመሰደድ መገደዳቸውን ለቤተሰቦቻቸው ገልፀዋል።

ወያኔ ዜጎችን እያፈሰና እየለቀመ በየእስር ቤቱ ከማጎሩም በላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ጥፋተኛ መሆናቸው ሳያረጋግጥ እና ውሳኔ ሳይሰጥበት ሽብርተኛ ናቸው ብሎ ፈርጆ እያስፈራራ ይገኛል። ከዚህም በላይ የወያኔ ተጠቃሚና አሽርጋጅ የሆኑት እነ ሽመልስ ከማል ያለ አንዳች ሀፍረት እና ይሉኝታ በዜጎቹ ላይ እየተሳለቁ መግለጫ በመስጠታቸው መላው የሀገሪቱ ዜጎች እጅግ ከማዘናቸውም በተጨማሪ ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ እንዳሉም ለማወቅ ተችሎዋል።

ዜጎች የእለት ጉርስ ለመሙላት እየተንከራተቱ ባለበት.....የኑሮ ጫናውን መሸከም አቅቶዋቸው እየተወዛወዙ በሚገኙበት በዚህ ግዜ......ከገጠሩ ነዋሪ እስከ ከተሜው......ከጎዳና ተዳዳሪው እስከ ተፈናቃዩ.....ከኢንቨስተር እስከ መንግስት ሰራተኛው .....ከመሀንዲስ እስከ ዶክተር .......ድረስ በጭንቀት ተወጥረው ስራ ከመስራት ይልቅ ይህንኑ ማሰላሰል ዋነኛ ተግባራቸው ሆኖ በመገኘቱ በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ የአዕምሮ መረበሽ እየተፈጠረ መሆኑን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

ሰሞኑን በተጀመረው የእስራት ዘመቻ ሳቢያ ዜጎች ከያሉበት ከመለቀማቸው በተጨማሪ ከህዝብ ማመላለሻ እና ህዝብ ከሚሰበሰብበት አዳራሾች ጭምር በደህንነቶች እና በፌዴራል ፖሊሶች ወከባና እንግልት እየደረሰባቸው እንደሚወሰዱ ለማየት ተችሎዋል።

ከመርካቶ ወደ ሳሪስ የምትጉዋዘው 29 ቁጥር የከተማ አንበሳ አውቶቡስ ውስጥ ህዝብ ሞልቶ በመጉዋዝ ላይ እንዳሉ ድንገት መትረየስ በተጠመደባት ፓትሮል አስቁመው መሀል አስፓልት ላይ ፍተሻ ከማድረጋቸውም በላይ ለግዜው ስሙና አድራሻው ያልታወቀ እድሜው 40ዎቹ ውስጥ የሚገኘውን ጎልማሳ እያዋከቡ አጣድፈው ከመውሰዳቸው በተጨማሪ ተሳፋሪውን በእርግጫና በጡጫ እየመቱ ሲያንገላቱዋቸው እንደነበረ የአይን እማኞች ገልፀዋል።የችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆነው የአዲስ አበባ ነዋሪም ሌት በውድቅት ቀን በጠራራ ፀሀይ በቅልብ የፌዴራል ልዩ ኮብራዎች በህዝብ ላይ የሚፈጸመውን አሰቃቂ ግፍ በያለበት ሆኖ እየተከታተለ ከመሆኑም በተጨማሪ አንደኛው ለሌላው እየተፈፀመ ያለውን መረጃ እየተለዋወጠ ህዝብ እንዲያውቀው እያደረገ እንደሚገኝ ታውቆዋል።

ወያኔ ፍጹም የህዝብ ድጋፍ እንደሌለው በማረጋገጡ የስልጣን እድሜውን ለማርዘም ሲል ብቻ የመሳሪያና የጦር ኃይሉን መከታ በማድረግ በዜጎች ላይ የከፋ እርምጃ በመውሰድ ላይ መሆኑንም ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ የተለያዩ ሀገራት ዲፕሎማቶችም እያረጋገጡ መሆኑ ታውቆዋል::

በ29 ቁጥር ውስጥ ተሳፍረው የነበሩና እንግልትና ወከባ ሲደረስባቸው የነበሩ ዜጎች ላይ የደረሰውን ግፍና ስቃይ ዲፕሎማቶቹ ሲከታተሉና በአነስተኛ የምስል መቅረጫ ሲቀርፁ እንደነበር የተስተዋሉ ሲሆን ይህም ታሪክ በቅርቡ በዓለም አደባባይ ላይ ይፋ ሊወጣ እንደሚችልም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል::

ህዝብ ወያኔን አይንህን ለአፈር ብሎ በጠላበት በዚህ ወቅት በግድ የስልጣን ዘመኑን ለማርዘም ሲል ብቻ ያልሆነ ስም እየለጠፈና ዜጎችን ጭንቀት ውስጥ እየከተተ በሚገኝበት በዚህ ግዜ በገዛ ካድሬዎቹም ላይ እምነት ስለሌለው በየጊዜው የሹም ሽር ከማድረጉም በተጨማሪ እርስ በርስ እንዲጠላለፉና እንዲቃረኑ እየሰራ መሆኑም ታውቆዋል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከበረሀ ጀምሮ በትግል ጉዋዶቹ ላይ ሲሰራበት የመጣውን ስልት አሁንም ድረስ እየተጠቃመበት ከመሆኑም በላይ አንዱ አንዱን ጠልፎ እንዲጥለውና እርስ በርስ መተማመን እንዳይኖር እያደረገ በመስራት ላይ ሲሆን በቅርቡም በሚደረገው የዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ካድሬዎች እርስ በርስ እንዲገማገሙ እንደሚደረግም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

በቅርቡ ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቀው የወያኔ ካድሬዎች ግምገማ ብአዴን፤ደኢህዴን፤ እና ኦህዴድ ውስጥ ሲሆን አነዚህ መሀከል እርስ በርስ ቅራኔ እንዲፈጠርና አንዱ ሌላኛውን እንዲያብጠለጥል እንደሚደረግ በዚህም መሀከል ለመለስ ምቹ የአገዛዝ ዘመን እንዲስምርለት ከፍተኛ ስራ እየተሰራ መሆኑ ተጠቁሞዋል::

ከተቃዋሚ ፓርቲ አባሎች ጋር ግንኙነት አላችሁ ፤ከውጭ ሀገር ካሉት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ጋር ግንኙነት አላችሁ ፤የሽብርተኝነት ህጉን ለህዝቡ በስፋት አላስረዳችሁም በሚሉና በሌሎችም ዙሪያ ካድሬዎቹን በግምገማ ሰበብ ወጥሮ መለስ እና ጥቂት ግለሰቦች ብቻ እንደልባቸው የሚጨፍሩበት የስልጣን ዘመን ለማደላደል ውስጥ ውስጡን እየተሰራ መሆኑም ታውቆዋል::

በቅርቡ በሱማሌ ክልል ባለስልጣናት ላይ ግምገማ ተደረገ ተብሎ የአመለካከት ችግር አለብህ......ከኦብነግ ጋር ግንኙነት አለህ እየተበሉ ከስልጣናቸው የተባረሩ ከመሆኑም በተጨማሪ በጅጅጋ ከተማ ውስጥ በቁም እስር ላይ እንዲቆዩ መደረጉ ታውቆዋል::

በአባይ ጸሀዬ መሪነት ሲደረግ የሰነበተው ይሄው ግምገማ አስቀድሞ ለወያኔ የማያሸረግዱ ተብለው በስም ዝርዝር ተለቅመው የተያዙ የዞንና የክልሉ ባለስልጣናትን የተለያዩ የስም ማጥፋት ዘመቻ ካደረጉ በሁዋላ ግምገማ በሚል ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ ማድረጋቸውን ያጋለጠው

የደረሰን ዘገባ በምትካቸው ሱማሊኛ ቁዋንቁዋ የሚናገሩ የሌላ ብሔር ሰዎች እንዲሾሙ መደረጉን የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

ስልጣን ላይ ከወጣ ከመለስ ዜናዊ እኩል እድሜ ያስቆጠረው የአፋር ክልል ፕሬዝዳንት እስማኤል አሊ ሴሮ በበኩሉ ሲወደስ እና ሲሞካሽ እንዳልነበር በቅርቡ ከእኛ እውቅና ውጭ የራስህን ቡድን መስርተሀል ተብሎ ተገምግሞ ሊባረር ጫፍ ላይ የደረሰ ቢሆንም እሱን የሚተካ ለመለስ ታማኝ የሆነ ሰው በመጥፋቱ በእንጥልጥል ላይ ብቻ ሆኖ እንዲቀር መደረጉንም የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል::

በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ለባለሀብቶች ከአፋር ክልል መሬት እየተቆረሰ መቸብቸቡን በተመለከተ የሽያጩ ገቢ ለእኛ መግባት ሲገባው ለፌዴራል ለምን ሆነ ብለህ ከመቃወምህም በላይ የራስህን ቡድን ፈጥረህ እየተንቀሳቀስክ ነው በሚል ተገምግሞ እንደነበርና ሊባረር የነበረ ቢሆንም የሚተካው ሁነኛ ሰው በመጥፋቱ ሳይወዱ በግድ በቦታው ላይ እንዲቆይ ማድረጋቸውን የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

በቤንሻንጉል ክልልም ከምክትል ፕሬዝዳንቱ እስከ ፀረ ሙስና ኮሚሽነሩ..... ከአፈ ጉባኤው እስከ ቢሮ ኃላፊዎች ድረስ የአመለካከት ችግር አለባችሁ ተብለው ከስልጣናቸው ከመነሳታቸው በተጨማሪ ገሚሶቹ ለእስር ሲዳረጉ የተቀሩት አምልጠው ደቡብ ሱዳን ጁባ መግባታቸውንም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

በጋምቤላ ክልል ውስጥም በተደረገ የማጥራት ዘመቻ ለ14 ዓመታት እና ከዚያም በላይ በቢሮ ኃላፊነት ሲሰሩ የነበሩትን አንስቶ ከአራት አመት ወዲህ ተመርጠው የፖለቲካ ኮርስ ሲሰጣቸው የነበሩ አዳዲስ እና ወጣት ካድሬዎች ቦታውን እንዲቆጣጠሩት መደረጉ ታውቆዋል::

በተለይ በኦህዴድ ውስጥ ሲብላላ የነበረውና ሁልግዜ በየዓመቱ በካድሬዎቹ የሚነሳው የስልጣን ባለቤትነት ጥያቄ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ እንዲያከትም በሚችልበት ሁኔታ ሊሰራ እንደሚችል እየተጠበቀ ሲሆን በብአዴን በኩልም ተመሳሳይ ስራ ሊሰራ ይችላል ተብሎ ይጠበቃል::

በአሁኑ ሰዓት በፍርሀት ውስጥ ተነክሮ እየዋለለ የሚገኘው የወያኔ ቡድን አማራጭ አድርጎ የያዘውና እየተጠቀመበት ያለው የሽብርተኝነት ታፔላ በዲፕሎማቶች ጭምር እየታወቀና እየተጋለጠ በመሄዱ በቅርቡ ደግሞ ሌላ አዲስ ስልት ሊያወጣ እንደሚችልም ከወዲሁ ግምቶች እየተሰነዘሩ ይገኛሉ::

የወያኔ ቡድን ባደረበት ፍርሀት የተነሳ በሲቪል ፖለቲከኞቹ ላይ የጀመረውን የምንጠራ ዘመቻ በቅርቡ ደግሞ ወደ መከላከያ ውስጥም ሊያሰርፀው በዝግጅት ላይ መሆኑ ታውቆዋል::

በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ የሚነሱ የአንድ ወገን የስልጣን የበላይነት ጥያቄ የተዳፈነ እየመሰለ ድንገት እየፈነዳ በማስቸገሩ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ በሚል እንደ ካድሬዎቹ ሁሉ በመከላከያ ውስጥም ምንጠራ ሊደረግ በዝግጅት ላይ መሆኑ ተጠቁሞዋል::

ልክ እንደ ብአዴን ኦህዴድና ሌሎቹም ካድሬዎች በመከላከያ ሰራዊት ውስጥም አማራውን ነፍጠኛ......ኦሮሞውን ሽብርተኛ...... ደቡቡን አጎብዳጅ.....እየተባለ የየራሳቸው ታፔላ

እየተለጠፈባቸው በግምገማ ሰበብ ከመባረራቸው በተጨማሪ ወደፊትም ጥያቄ ሊያነሱ ይችላሉ የሚባሉትን ለእስር ሊዳርጉ እንደሚችል እየተነገረ ይገኛል፡፡

በሰራዊቱ ዘንድ ተቀባይነት አላቸው..... ከስራ ቢባረሩ አስጊ ናቸው የተባሉት ነባር መኮንኖች አሁን ተመድበው ከሚሰሩበት የጦር ክፍል ተነስተው ወደ ተለያዩ ክፍሎች እንዲመደቡ እንደሚደረግ የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በተለይ የብአዴን ታጋይ የነበሩት መኮንኖች በሽብርተኝነት ሊከሰሱ እንደተዘጋጀም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡